# ኮሮና ቫይረስ 2019 (COVID-19)፣
# የሰለጡኑ ነርሶች ተቋማት እና ድጋፍ የሚደረግላቸው የመኖሪያ ቤቶችን የቤት ውስጥ ጉብኝት መስፈርቶች

ይህ ሰነድ በCMS መመሪያዎች መሰረት በደረጃ ሁለት ወቅት በኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ የሰለጠኑ ነርሶች ተቋማት እና ድጋፍ የሚደረግላቸው የመኖሪያ ቤቶችን የቤት ውስጥ ጉብኝት መስፈርቶችን ይሰጣል (cms.gov/files/document/qso-20-39-nh.pdf)። የቤት ውስጥ ጉብኝቶች ሲደረጉ የCOVID-19 የተጋላጭነት አደጋን ለመቀነስ የሚከተሉት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በከንቲባ ትእዛዝ 2020-063 ላይ በተደነገገው መሠረት የጉብኝት ገደቦች ለተንከባካቢዎች ወይም አስፈላጊ ጎብኚዎች ወይም ባለሟሎች ተፈጻሚ አይደለም።

## የቤት ውስጥ ጉብኝት መጠየቅ የሚቻልበት መስፈርቶች

- በተቻለ መጠን ከቤት ውስጥ ጉብኝት ይልቅ የውጭ ጉብኝት ተመራጭ ነው።
- ተቋሙ በDC Health መስፈርቶች መሰረት ሳምንታዊ የሰራተኛ ምርመራ ማድረግ አለበት እና ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት 90% ውጤታማ መሆን አለበት።
- ተቋሙ በየቀኑ ከሰኞ-አርብ በዓላትን ጨምሮ የCOVID-19 የመስመር ዝርዝር ለጤና እንክብካቤ ተቋማት የምርመራ ቡድን **በመደበኛነት** ማቅረብ አለበት።
- ከሰራተኛ ወይም ከኗሪዎች ውስጥ አንድም ቢሆን COVID-19 የተገኘባቸው ተቋማት የቤት ውስጥ ጉብኘት ለመጀመር/ለመቀጠል ከDC Health COVID-19 የጤና እንክብካቤ ተቋም ቡድኖች ፍቃድ ማግኘት አለባቸው። የሚከተለው መስፈርት ቢያንስ መሟላት አለበት፣
    - በተቋሙ ውስጥ በኗሪዎች ቢያንስ ለሁለት ተከታታይ ሳምንታት ምንም አዲስ የCOVID-19 ጉዳዮች መኖር የለበትም።
    - በተቋሙ ውስጥ ለሁለት ሳምንታት በኤፒዲሚዮሎጂክ ምርምራ(ለምሳሌ፣ ቅደም ተከተል)መሰረት የተለዩ 3 ወይም ከዚያ በላይ ከአንድ ክፍል ወይም ከመላው ተቋም ጋር የተያያዘ የወረርሽኝ ጉዳይ መኖር የለበትም።
- ተቋሙ ከተረጋገጠ ወይም ከተጠረጠረ ወረርሽኝ ጋር በተያያዘ ምርመራ እያደረገ መሆን የለበትም።
- ተቋማት ያለአንዳች ጥገኝነት ወይም በህዝብ ጤና ከምችት ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ ለወረርሽኙ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የሁሉም የግል መጠበቂያ መሳሪያ (personal protective equipment, PPE) የ14 ቀን አቅርቦት ሊኖራቸው ይገባል።
- ተቋማት ከታች ያሉትን ሁኔታዎች የሚገልጹ እና ለጉብኝት የተለየውን ስፍራ በተመለከተ ዝርዝር እቅድ ለDC Health ማቅረብ አለባቸው።
    - ከ1 በላይ የጎን ግድግዳ ያላቸው ድንኳኖች ቤት ውስጥ ተደርገው የሚቆጠሩ መሆኑን እባክዎ ያስታውሱ።

## የቤት ውስጥ ጉብኝት ከመጠየቅዎ በፊት

- ለኗሪ ቤተሰቦች በተቋሙ ውስጥ የቤት ውስጥ ጉብኝት እየተከናወነ መሆኑን ያሳውቋቸው። ማስታወቂያው የሚከተለውን ማካተት አለበት፣
    - የኗሪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የተወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች።
    - በጉብኝት የሚጠበቁ ነገሮች እና መስፈርቶች። ማስታወቂያው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፣
        - የምልክት ማጣሪያ ሂደት መግለጫ።
        - የጭምብል እና የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶች፣ አስፈላጊ ሲሆን ሰራተኛን እንዴት መጥራት እንደሚቻል፣ እና ጎብኚ እንዳይገባ የሚከለከልበት ምክንያትን ጨምሮ የቤት ውስጥ እና የውጭ ጉብኝቶች ሁሉም የስምምነት ግዴታዎች።
        - ጎብኚዎች ከጉብኝታቸው በፊት፣ ሲደርሱ፣ እና በጉብኝት ወቅት ማድረግ ያለባቸው ነገሮች።
- ተቋሙ የሰራተኞች እና የኗሪዎች የCOVID-19 ማጣሪያ እና ክትትል መስፈርቶቹን እያሟላ መሆኑን ማረጋገጥ።

## የቤት ውስጥ ጉብኘት ሲጀምር

- የቤት ውስጥ ጉብኝትን የጭምብል እና የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶቹን ለሚያከብሩ ጎብኚዎች ብቻ ይፍቀዱ።
    - እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆኑ ህጻናት ሁሉጊዜ በሞግዚታቸው መታጀብ አለባቸው እና የፊት መሸፈን እና የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶችን ማክበር አለባቸው።
- በአንድ ጉብኝት ወቅት ጎብኝዎች ከአንድ ቤተሰብ ብቻ መሆን አለባቸው።
- በአንድ ጉብኝት ወቅት፣ ጎብኚዎች በስፍራው ቆይተው በርካታ ኗሪዎችን እንዲጎበኙ ሊፈቀድላቸው አይገባም።
- ጉብኝቶች ከ30 ደቂቃ በላይ ሊበልጡ አይገባም።
- ተቋሙ ደህንነት በተጠበቀ ሁኔታ ሰዎችን እንዲያስተናግድ እና የጥንቃቄ እርምጃዎች መተግበራቸውን ለመቆጣጠር በቂ ሰራተኞች እንዲኖረው ለማስቻል ጎብኚዎች አስቀድመው ለጉብኝት ቀጠሮ እንዲያስይዙ ይጠይቁ።
- ጎብኚዎችን በመግቢያው ላይ በተለየ አንድ ቦታ ላይ ይቀበሏቸው፣በዚህም ወቅት የተቋሙ ሰራተኛ የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፣
    - ሁሉንም ጎብኚዎች እና አገልግሎት አቅራቢዎች መመርመር።

- የሙቀት ምርመራ እና የምልክት ማጣሪያን ማከናወን።
- ጎብኚዎች ከትኩሳት ነጻ፣ከምልክቶች ነጻ፣ እና ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ COVID-19 ላለበት ሰው ተጋላጭ ያልነበሩ መሆን አለባቸው።
- ጎብኚዎች በcoronavirus.dc.gov/phasetwoላይ በተገለጸው መሰረት ከፍተኛ ስጋት ወዳለው ክልል ፣ወይም በDC Health የጉዞ መመሪያ ላይ በተገለጸው መሠረት ወደ ደረጃ 3(ከፍተኛ ስጋት)ሀገር በተደረገ አስገዳጅ ባልሆነ ጉዞ ምክንያት በማግለል(ኳረንቲን)ላይ መሆን የለባቸውም።
- ለማጣሪያ መሳሪያ መምሪያ፣ይጎብኙ coronavirus.dc.gov/healthguidance.

  - ጎብኚው የትንፋሽ ማስወጫ የሌለው የፊት ጭምብል ወይም የጨርቅ መሸፈኛ ማድረጋቸውን፣እና ጭምብሉ የጎብኚውን አፍንጫ እና አፍ መሸፈኑን ያረጋግጡ።
  - ጎብኚው ወደ ተቋሙ ሲገቡ እና ሲወጡ እጃቸውን አልኮል ባለው የእጅ ሳኒታይዘር እንዲያጸዱ ያድርጉ።
- የጎብኚውን ሙሉ ስም፣የስልክ ቁጥር፣የተሟላ የቤት አድራሻ፣ኢሜይል፣የሚጎበኙትን ሰው የክፍል ቁጥር እና ስም መዝግበው ይያዙ፣እና ይህን ሪከርድ ንኪኪን ለመለየት እንዲረዳ ለ30 ቀናት ያያዙት።
  - ተቋሙ ይህ ጥያቄ ሲቀርብለት በ12 ሰዓታት ውስጥ ይህን መረጃ ለDC Health መስጠት መቻል አለበት።
- ሰራተኞች ወደተመደበው የጉብኝት ቦታ ጎብኚውን ማጀብ አለባቸው።
  - ጎብኚዎች ወደ ተቋሙ ሌላ ማንኛውም ክፍል መግባት አይፈቀድላቸውም።
- ምርመራው ያላለፉ ወይም ማናቸውንም መስፈርቶች ለማክበር ፍቃደኛ ያልሆኑ ጎብኚዎችን ወይም አገልግሎት አቅራቢዎችን እንዳይገቡ ይከልክሉ።

## በቤት ውስጥ ጉብኘት ወቅት

- ጎብኚዎች በጉብኝቱ ወቅት በሙሉ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ ወይም ጭምብል ማድረግ እና ከኗሪው የ6 ጫማ ርቀት መጠበቅ አለባቸው።
- ጎብኚዎች ጉብኝቱ እንዲካሄድ የተመደበበት ስፍራ ላይ ብቻ መወሰን አለባቸው።
- ጎብኚዎች ሊጎበኙት ያቀዱትን ኗሪ ብቻ በተመደበው የጉብኝት ስፍራ መጎብኘት አለባቸው።
- ኗሪዎች ወደ ጉብኝት ስፍራው ሲሄዱ እና ሲመለሱ ጨምሮ በጉብኝቱ ሁሉም ጊዜያት የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ወይም የፊት ጭምብሎችን እንዲያደርጉ በጥብቅ ይመከራሉ።
- የቤት ውስጥ ጉብኝትን ተገቢ ማህበራዊ ርቀትን የሚፈቅዱ ቦታዎች ላይ ይገድቡ።
  - ቦታው ተገቢ የአየር ዝውውር(ክፍት መስኮቶች፣ ወዘተ)ሊኖሩት ይገባል።
  - ቦታው ለኗሪዎች እና ለተለዩት ጎብኚዎቻቸው ብቻ መለየት አለበት።
  - ከሌሎች ኗሪዎች ጋር ተጋላጭነትን ሊቀንሱ የሚችሉ ወደ ተመደበው የጉብኝት ቦታ የተለዩ መግቢያዎች፣ መውጫዎች፣እና መንገዶች ሊኖር ይገባል።
  - የሚፈቀደው የጎብኚዎች ቁጥር የማህበራዊ ርቀት መስፈርቶችን ጠብቆ ለማስተናገድ ከሚያስችለው አቅም መብለጥ የለበትም።
  - የጉብኝት ስፍራው በአንድ ጉብኝት ወቅት ለአንድ ቡድን ጎብኚዎች እና ኗሪው አገልግሎት ብቻ መዋል አለበት።
  - አማራጭ ካልታጣ በስተቀር፣ ኗሪዎች በጋራ የሚጠቀሙባቸውን የእንቅስቃሴ ስፍራዎችን (ለምሳሌ፣ የእራት መመገቢያ ክፍሎች) አለመጠቀምን እንመክራለን።
- የነዋሪዎቹ ክፍሎች ለጉብኝት ቦታ አገልግሎት ሊሰጡ የሚገባው ለቤት ውስጥ ጉብኝት የተመደበው ቦታ ለኗሪዎች ተደራሽ ሳይሆን ሲቀር ብቻ ነው።
  - ይህ ሊሆን የሚገባው የግል ክፍል ላይ ብቻ ነው።
  - ጎብኚዎች መታጠቢያ ክፍሎችን ጨምሮ የኗሪዎችን መኖሪያዎችን መጠቀም የለባቸውም። ከዚያ ይልቅ ኗሪዎች ወደማይጠቀሙባቸው መታጠቢያ ቤቶች መሄድ አለባቸው።
  - ጉብኝቱ ሲጠናቀቅ መጸዳት እና ዲስኢንፌክት መደረግ አለበት።

## ከቤት ውስጥ ጉብኝት በኋላ

- ጎብኚው ከተቋሙ ሲወጡ እጃቸውን አልኮል ባለው የእጅ ሳኒታይዘር እንዲያጸዱ ያድርጉ።
- ለጉብኝት የተመደበው ስፍራ ከእያንዳንዱ ጉብኝት በኋላ መጸዳት እና ዲስኢንፌክት መደረግ አለበት።
- ተቋሙ በከፍተኛ ሁኔታ የሚነኩ ስፍራዎችን (ለምሳሌ፣ ማብሪያ እና ማጥፊያዎች፣ የኤሊቬተር ቁልፎች፣የበር እጀታዎች) በፈረቃ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጊዜ ማጽዳት እና ዲስኢንፌክት ማድረግ አለበት።
- ጉብኝቶቹ እስኪጠናቀቁ እና ቦታው ተጸድቶ ዲስኢንፌክት እስኪደረግ ድረስ ማንኛውም ኗሪ ወደ ቦታው እንዲመጣ ሊፈቀድለት አይገባም።

## የCOVID-19 ተጋላጭነት ማስታወቂያ

- ተቋሙ ጎብኚዎች ከጉብኝቱ ቀን አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ ለCOVID-19 ተመርምረው ፖዘቲቭ ቢሆኑ ተቋሙን የሚያሳውቁበት አድራሻ እና ተጨማሪ መመሪያዎችን የያዘ መረጃ ለሁሉም ጎብኚዎች መስጠት አለበት።

- የተቋሙ ሰራተኞች ኗሪው የሚኖሩበት ክፍል ውስጥ ጉብኝቱ በተደረገ በ14 ቀናት ውስጥ ወረርሽኝ ከተከሰተ፣ ለጎብኚዎች ማሳወቅ እና ጎብኚው(ዎቹ) እንዲመረመሩ መምከር አለባቸው።

### ማግለያዎች

- የፊት መሸፈኛ፣የማህበራዊ ርቀት፣እና ሌሎች የተቋም መስፈርቶችን ማክበር የማይችሉ ጎብኚዎች የቤት ውስጥ እና የውጭ ጉብኝቶች ላይ መሳተፍ የለባቸውም።

ወረርሽኙ ሲቀያየር ከዚህ በላይ ያሉት መመሪያዎች መሻሻላቸውን ይቀጥላሉ። እባክዎ በጣም ለቅርብ ጊዜ መረጃ coronavirus.dc.gov ይጎብኙ።